# የማኪኒ-ቬንቶ (McKinney-Vento) መርኃ ግብር የተማሪ ሪፈራል

የትምህርት ዘመን 20________- 20

## ክፍል 1፡- ማጣርያ [ በወላጅ ወይም በአሳዳጊ መሞላት ያለበት]

*የአርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች የማኪኒ-ቬንቶ (McKinney-Vento) ከፌዴራል የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኝ እና በማኪኒ-ቬንቶ (McKinney-Vento) የቤት አልባ ትምህርት እርዳታ ህግ ስር የመኖርያ ቤት አልባ ለሆኑ ልጆች እና ታዳጊዎች ተገቢውን የህዝብ ትምህርት እና ልምድ የማግኘት ሙሉ እና እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያረጋገጥ መርኃ ግብር ነው። የዚህ ቅጽ አላማ፣ በAPS ውስጥ የመኖርያ ቤት አልባ የሆኑ ተማሪዎችን መለየት እና መደገፍ ነው። እባክዎ በዚህ ቅጽ ላይ ያለው መረጃ **ሚስጥራዊ** መሆኑን ይወቁ። ስለ ማኪኒ-ቬንቶ (McKinney-Vento) አገልግሎቶች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎን የAPS ድህረ ገጽን [https://www.apsva.us/departments/dei-student-support/mckinney-vento/](https://www.apsva.us/departments/dei-student-support/mckinney-vento/) ይጎብኙ ወይም በ(703) 228-6046 ይደውሉ።*

**የማኪኒ-ቬንቶ (McKinney-Vento) ድጋፍ ለማግኘት ብቁ መሆንዎን ለመወሰን እባክዎ ለሚከተሉት የማጣሪያ ጥያቄዎችን መልስ ይስጡ፥**

1. ያሁኑ አድራሻዎ ጊዜያዊ የመኖሪያ አደረጃጀት ነው? ከሆነ፣ በመኖሪያ ቤት አልባነት ወይም በኢኮኖሚ ችግር ምክንያት ነው? ☐ አዎ ☐ አይ
2. ተማሪው የሚኖረው ከወላጆቹ ወይም ከህጋዊ አሳዳጊ ውጪ ከሌላ ሰው ጋር ነው? ☐ አዎ ☐ አይ

ከላይ ላሉት **ሁለቱም** ጥያቄዎች **አይ** ብለው ከመለሱ፣ እዚህ ያቁሙ። **ይህንን ቅጽ መመለስ ኣይጠበቅብዎትም።**

ከሁለቱ **እንዱንም** ቢሆን **አዎ** ብለው ከመለሱ፣ ለመኖሪያ ቤት አልባነት የድጋፍ አገልግሎቶች ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። እባክዎት **ክፍል 2ን በሞምላት ይህንን ቅጽ ወደ ትምህርት ቤትዎ ጽህፈት ቤት ይመልሱ።**

## ክፍል 2፡- የተማሪ መረጃ

የወላጅ ወይም አሳዳጊ ስም (ስሞች) ________________________________________

አድራሻ ________________________________________

መንገድ　　アパートメント # 

የቤት ስልክ ቁጥር________________ የስራ ስልክ ቁጥር ________________ የእጅ ስልክ ________________

ኢሜል ________________________ ተመራጭ ቋንቋ (ከእንግሊዘኛ ውጪ ከሆነ) ________________

| ስም (እባክዎ በቤተሰቡ ስር ያሉት የሁሉም ልጆች ስም ዝርዝር ይጻፉ) | የትውልድ ቀን | ክፍል | ትምህርት ቤት | የተማሪ ቁጥር # |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |

አሁን የሚኖሩት የት ነው?

- ☐ በኢኮኖሚ ችግር፣ በመኖርያ ቤት አልባነት ወይም ተመሳሳይ ችግሮች ምክንያት ተዳብየ እና/ወይም ከአንድ ቤት ወደ ሌላ ቤት በመዘዋወር
- ☐ በቂ አማራጭ በማጣት ምክንያት ሞቴል ወይም ሆቴል ውስጥ – የሞቴል ወይም ሆቴሉ ስም________________
- ☐ የመኖርያ ቤት አልባነት መጠለያ ወይም የቤት ውስጥ ጥቃት ፕሮግራም - የአገልግሎት ሰጪው ስም________________
- ☐ የሽግግር መኖሪያ - የአገልግሎት ሰጪው ስም ________________
- ☐ እንደ መኪና፣ መናፈሻ ወይም የካምፕ ቦታ ለመኝታ ቤቶች ባልተዘጋጀ ቦታ________________

**ልጄ(ልጆቼ) በአርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች (ኤፒኤስ) መመዝገብ እኔ በምሰጠው ቃል ላይ የተመሰረተ መሆኑን ተረድቻለሁ፣ ቃሌ ውሸት ከሆነ፣ ለልጄ (ልጆቼ) ሙሉ ክፍያ የመክፈል ሀላፊነት እንዳለብኝ ተረድቻለሁ። በ§22.1-264.1<u>የቨርጂኒያ ኮድ</u> ስር፣ ማንኛውም ሰው እያወቀ የትምህርት ክፍያን ለማስቀረት የልጅን ነዋሪነት በተመለከተ የውሸት ቃል የሰጠ በክፍል 4 ጥፋተኛ ይሆናል። የራሴ ወይም የልጄ (ልጆቼ) የመኖሪያ ለውጥ በተደረገ በሶስት (3) ቀናት ውስጥ ለርእሰ መምህሩ ወይም ለተወካዩ ለማሳወቅ ተስማምቻለሁ።**

☐ **የመኖርያ ቤት አልባ ተማዎች መብቶችን** ተቀብያለሁ።

________________________________________ ________________

**የወላጅ/አሳዳጊ ፊርማ (*አሰፈላጊ*)** **ቀን**

**የትምህርት ቤት ምዝገባ** ክፍል፡- የተሞሉ ቅጾችን ወደ ትምህርት ቤቱ ማህበራዊ ሰራተኛ ይስጡ ወይም ስካን በማድረግ ወደ elizabeth.ryan@apsva.us ኢሜል ያድርጉ።

**የአርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች – የተማሪዎች አገልግሎቶች ጽህፈት ቤት**

**የማኪኒ-ቬንቶ (McKinney-Vento) መርኃ ግብር**

## የመኖርያ ቤት አልባነት ችግር ያጋጠማቸው ተማሪዎች መብቶች

የአርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች (APS) ሁሉንም ተማሪዎች በክብር እና በአክብሮት የሚይዝ የትምህርት አካባቢ መፍጠር አለባቸው። እያንዳንዱ የAPS የመኖርያ ቤት አልባ ተማሪ ይህንን ችግር ከሌለባቸው ተማሪዎች ጋር እኩል የሆነ ነፃ እና ተገቢ የትምህርት እድሎችን የማግኘት መብት አለው። ይህ የመኖርያ ቤት አልባ ለሆኑ ህጻናት፣ ታዳጊዎች እና ከወላጅ ወይም አሳዳጊ ጋር ለማይኖሩ ታዳጊዎች የትምህርት መብቶች ለሁሉም አገልግሎቶች፣ መርኃ ግብሮች እና በኤፒኤስ የሚሰጡ ወይም የሚገኙ ተግባራት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

አንድ ተማሪ **የማኪኒ-ቬንቶ** (McKinney-Vento) መስፈርቶች የሚያሟላ:-

- በኢኮኖሚያዊ ችግር ምክንያት ወይም በመኖርያ ቤት አልባነት ለጊዜው ከሌላ ሰው ጋር ተዳብሎ የሚኖር ከሆነ
- በበቂ ተመራጭ የመስተንግዶዎች እጦት ምክንያት፣ ለጊዜው ሞቴሎች ወይም ሆቴሎች ውስጥ የሚኖር ከሆነ
- በድንገተኛ የመኖርያ ቤት አልባ መጠለያ ወይም የቤተሰብ መጠልያ ውስጥ የሚኖር ከሆነ
- የሽግግር መኖርያ ቤት ውስጥ የሚኖር ከሆነ
- ባልተጠለሉ ቦታዎች እንደ መኪና፣ መናፈሻ ወይም የካምፕ ቦታ የሚኖር ከሆነ
- ከቤተሰብ ጋር የማይኖር እና የመኖርያ ቤት አልባ የሆነ ታዳጊ ከሆነ ነው።

**<u>የመኖርያ ቤት አልባነት ችግር ያጋጠማቸው ተማሪዎች ተማሪዎች የሚከተሉት መብቶችን አሉዋቸው:-</u>**

- **ወዲያውኑ የትምህርት ቤት ምዝገባ:-** የጤና፣ የክትባት ወይም የትምህርት ቤት መዛግብት፣ የአሳዳጊነት ማረጋገጫ፣ ወይም የመኖሪያ ፈቃድ ባይኖራቸውም ትምህርት ቤቱ ወዲያውኑ ተማሪዎችን መመዝገብ አለበት።

- **የሚመዘገቡበት ትምህርት ቤቶች :-**
  *በቋሚነት በሚኖርበት ጊዜ የሚማሩበት በነበረው ትምህርት ቤት (አጎራባች ትምህርት ቤት)
  *ለመጨረሻ ጊዜ የተመዘገቡበት ትምህርት ቤት (አጎራባች ትምህርት ቤት)
  *ቤት አልባ ያልሆኑ ልጆች በሚኖሩበት በተመሳሳይ የመኖርያ አከባቢ ውስጥ የሚኖሩ የመኖርያ ቤት አልባ የሆኑ ተማሪዎች ወይም ታዳጊዎች በትምህርት ቤቶቹ ለመማር ብቁ ናቸው።

- ተማሪው የመኖርያ ቤት አልባ ሆነው እስከቆዩ ድረስ ወይም በቋሚነት መኖርያ ቤት ካገኙ እስከ የትምህርት አመቱ መጨረሻ ድረስ በመረጡት ትምህርት ቤት **እየተማሩ ይቆያሉ።**

- **በአንዳንድ የቅድመ ትምህርት መርኃ ግብሮች ቅድምያ:-** ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች በነዚህ መርኃ ግብሮች ላይ ለመሳተፍ እንዲጠይቁ ይበረታታሉ።

- ክፍያ ማስቀረትን፣ ነጻ ዩኒፎርሞችን፣ በዝቅተኛ ወጪ ወይም ነጻ የህክምና ሪፈራሎችን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ **መረጃ የማግኘት።**

- **የመጓጓዣ አገልግሎቶች:-** የመኖርያ ቤት አልባ የሆኑ ተማሪ፣የመኖርያ ቤት አልባ ሆኖው እስከቆዩ ድረስ ወይም ቋሚ የሆነ የመኖርያ ቤት ካገኙ ደግሞ እስከ የትምህርቱ አመት መጨረሻ፣ ከ እና ወደ የሚማሩበት ትምህርት ቤት የመጓጓዛ አገልግሎት የማግኘት መብት አሉዋቸው። የAPS ሰራተኞች መኖርያ ቤት አልባ ለሆኑ ወላጆች/አሳዳጊዎች ወይም ወጣቶች ከ እና ወደ ትምህርት ቤት እና ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ የመጓጓዣ አገልግሎቶችን ማሳወቅ አለባቸው።

ስለ መኖርያ ቤት አልባ ልጆች ወይም ታዳጊዎች ምዝገባ፣ መጓጓዣ ወይም ፍትሃዊ አያያዝ ከትምህርት ቤት ባለስልጣናት ጋር ካልተስማሙ ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ። የክርክር አፈታት ሂደትን በሚመለከት የተማሪዎች አገልግሎቶች ክፍለ ትምህርትን በስልክ ቁጥር 703-228-6046 በማነጋገር መረጃ ማግኘት ይቻላል።